የ8ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መርሀ ትምህርት

1. **የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 12**

- የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነትን ይገነዘባሉ።
- የዜጐችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይረዳሉ።
- የዴሞክራሲ ተቋማት አስፈላጊነትን ይረዳሉ።
- ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖርን አስፈላጊነቶችንና ጠቀሜታን ይረዳሉ።
- የፌዴራል እና የክልል መንግሥታትን አንድነትና ልዩነት ያውቃሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶችን ይዘረዝራሉ፣ | 1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነት፣<br>1.1.2 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶች፣<br>- የሕዝቦች መፈቃቀድና የዜጐች መበት መጠበቅ፣<br>- የእኩልነት መብቶች መከበር፣<br>- የመምረጥና የመመረጥ መብት፣<br>- በራስ ቋንቋ የመጠቀም መብት መከበር፣<br>- የመሰብሰብ የመናገርና የመጻፍ መብቶች መከበር፣ | • የዴሞክራሲ ሥርዓት የዜጐች መብትና ነፃነት የሚያስከብር ሥርዓት ነው። እንዲህ እያሉ ተማሪዎች ስለዴሞክራሲ ሥርዓት ምንነት በየተራ እንዲያብራሩ ማድረግ።<br>• በይዘትነት የተመለከቱትን ርዕሰ ጉዳዮች በቡድን በማከፋፈል የይዘቶቹን ምንነትና እንዴት የዴሞክራሲ መሠረቶች እንደሚሆኑ ተወያይተው ለክፍል እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ | 1.2 የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ | • ለክለሳ እንዲረዳ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከፌዴራል ሕገመንግሥት |

የ8ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| መብቶች መከበር የሚሰሩ ተቋማትን ይዘረዝራሉ፣<br>• የተቋማቱን አስፈላጊነት ይገልፃሉ። | መብቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትና አስፈላጊነታቸው፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>- የዜጎች መብቶች እንዳይጣሱ ተፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣ | አንፃር ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ። ከዚያም በቡድን ተከፋፍለው የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለምን ጥበቃ እንደሚደረግላቸው እንዲሁም ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ የሚያደርጉ ተቋማት እነማን እንደሆኑ እንዲወያዩባቸውና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። እንዲሁም በአካባቢያቸው የሚገኙ ተቋማትን (ለምሳሌ ፍርድ ቤቶችን፣ ፖሊስ ጣቢያዎችን ወዘተ) በመጐብኘት ተቋማቱ እንዴት ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ እንደሚያደርጉና አስፈላጊነታቸው ላይ የጋራ መግባባት እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ልዩነቶች/ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣<br>• ከጓደኞቻቸው ጋር የሚገጥማቸውን አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ይፈታሉ፣ | 1.3 ልዩነቶችን/አለመግባባቶችን በሰላም የሚፈቱባቸው መንገዶች ፣<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>-መወያየት፣<br>-መደማመጥ፣<br>-መቻቻል፣ | • ወደ ግጭት ሊወስዱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ጉዳዮችን (Case studies) ለተማሪዎች በቡድን ከፋፍሎ በመስጠት እነዚህን ችግሮች እንዴት እንደሚያስወግዱአቸው እንዲወያዩባቸውና የውይይታቸውንም ጭብጥ ለክፍል በማቅረብ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሥልጣን ይገልፃሉ፣<br>• የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣን የሆኑትን ይለያሉ፣<br>• የከተማ አስተዳደሮችን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ | 1.4 የፌዴራልና የክልል መንግሥታት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.4.1 አንድነትና ልዩነት፣<br>1.4.2 የጋራ ሥልጣን፣<br>1.4.3 የከተማ አስተዳደሮች ዋና ዋና ተግባራት፣ | • ሦስት ቡድኖችን በመመሥረት አንዱ ቡድን የፌዴራል መንግሥቱን መዋቅር በካርቶን ላይ ሰርቶ እንዲመጣ፣ ሌላኛው የራሱን ክልላዊ መንግሥት መዋቅር እንዲሁ ሰርቶ እንዲመጣ፡ ሦስተኛው ደግሞ ከፌዴራል ሕገመንግሥቱ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣን የተባሉትን ለቅሞ እንዲመጣ የቤት ሥራ መስጠት፣ እያንዳንዱ ቡድን በተዘጋጀው መሠረት ዝግጅቱን ለክፍሉ እንዲያቀርብ ማድረግና የጋራ መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ሰላማዊ ግንኙነት የሚሰጣትን ጥቅም ያብራራሉ፣ | 1.5 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.5.1 ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት፣<br>1.5.2 ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ባላት ግንኙነት | • ትምህርቱን በሰላም አብሮ የመኖር ጠቀሜታን አጉልቶ በማሳየት መጀመር። ለምሳሌ አንድ ተማሪ ከሌሎች ጋር በሰላም ተግባብቶ የሚኖር ከሆነ ከጓደኞቹ ጋር አብሮ በማጥናት በትምህርቱ ውጤታማ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በማቅረብ በሰላም አብሮ መኖር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ተማሪዎቹ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ። የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ዓላማ ከሀገራት ጋር በሰላም አብሮ መኖር ነው። ስለዚህ ተማሪዎቹን በቡድን |

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
| --- | --- | --- |
| | የምታገኘው ጥቅም፣ | በመክፈል ይህ የኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር በሰላም አብሮ መኖር ዓላማ ሀገሪቱን እንዴት ሊጠቅማት እንደሚችል እንዲወያዩበትና ድምዳሜያቸውን ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ መካከል የሚታየውን የውጤት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነትን ይዘረዝራሉ፣የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶችን ይዘረዝራሉ፣ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚሰሩ ተቋማትን ይዘረዝራሉ፣የተቋማቱን አስፈላጊነት ይዘረዝራሉ።ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚሰሩ ተቋማትን ይዘረዝራሉ፣የተቋማቱን አስፈላጊነት ይገልፃሉ።ልዩነቶች/ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣ከጓደኞቻቸው ጋር የሚገጥማቸውን አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የመፍታትን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሥልጣንን ይዘረዝራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣን የሆኑትን ይዘረዝራሉ፣የከተማ አስተዳደሮችን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ሰላማዊ ግንኙነት የሚሰጣትን ጥቅም ያብራራሉ፣
**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምንነትን ይገልፃሉ፣የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቶችን ይዘረዝራሉ፣ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚሰሩ ተቋማትን ይዘረዝራሉ፣የተቋማቱን አስፈላጊነት ይገልፃሉ።ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚሰሩ ተቋማትን ይዘረዝራሉ፣የተቋማቱን አስፈላጊነት ይገልፃሉ።ልዩነቶች/ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣ከጓደኞቻቸው ጋር የሚገጥማቸውን አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ይፈታሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሥልጣን ይገልፃሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ሥልጣን የሆኑትን ይለያሉ፣የከተማ አስተዳደሮችን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ያላት ሰላማዊ ግንኙነት የሚሰጣትን ጥቅም ያብራራሉ፣
**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 2. የሕግ የበላይነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- በፌዴራል ሕገመንግሥትና በክልል ሕገመንግሥት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ያውቃሉ።
- የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነት ይረዳሉ።
- የሚጠበቅባቸውን ሥነምግባር ያውቃሉ።
- ሙስና የሚያስከትላቸውን ችግሮች ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥትና በክልል ሕገ መንግሥታት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ይተነትናሉ፣ | 2.1 ሕገ መንግሥት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)** 2.1.1 የኤፌዴሪ ሕገ መንግሥትና የክልል መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች አንድነትና ልዩነት፣ | • ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን በመክፈል አንደኛው ቡድን የክልሉን ሕገመንግሥት እንዲመረምር ማድረግ። ሌላኛውን ቡድን ደግሞ የኤፌዴሪን ሕገመንግሥት እንዲመረምር ማድረግ። ለምሳሌ በሁለቱ ሕገ መንግሥቶች የሰፈሩት መግቢያዎች ልዩነታቸው ምንድን ነው? ፣ የሕገመንግሥት መርሆዎችን በተመለከተ ያሏቸው ልዩነቶች ምንድን ናቸው? የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በተመለከተ ያሏቸው ልዩነቶች ምንድን ናቸው? ወዘተ። ግኝታቸውንም ለክፍል በማቅረብ ሁለቱ ሕገመንግሥቶች ያሏቸውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • በሀገር ደረጃ ከተማሪ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይዘረዝራሉ፣ | 2.2 ሥነምግባር፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)** 2.2.1 በሀገር ደረጃ ከተማሪ የሚጠበቅ ሥነምግባር፣ - የሀገርን ሕገመንግሥትና ሌሎች ሕጐችን ማክበር፣ - ከማናቸውም ሕገወጥ ተግባራት መታቀብ፣ | • በዝቅተኛ ክፍሎች የተማሯቸውን ሥነምግባሮችን መከለስ። በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል እንደ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው በሀገር ደረጃ ከነሱ የሚጠበቀው ሥነምግባር ምን እንደሆነ ተወያይተው ለክፍል እንዲያቀርቡና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ውይይታቸው በተጠቀሱት ይዘቶች ዙሪያ እንዲሁን ፍረት ማድረግ። |
| • የሥልጣን ገደብ አለመኖር | 2.3 የሥልጣን ገደብ፣ | • በዚህ የክፍል ደረጃ የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ጠንቅቀው እንደሚያውቁ ይታመናል። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| የሚያስከትላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣<br>• የሚያከናወኗቸውን ተግባራት ባላቸው መብት ዙሪያ ብቻ ያደርጋሉ። | (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.3.1 የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሚያስከትላቸው ችግሮች፣<br>- በዘፈቀደ መሥራት፣<br>- የማን አለብኝነት ስሜት መጐልበት፣<br>- ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ | ስለሆነም አወያይና አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን (Case Studies) በቡድን ከፋፍሎ በመስጠት የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሚያስከትለውን ችግር በተመለከተ ተወያይተው የራሳቸውን ድምጻሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የሚስጥር መባከን በሀገር ደረጃ ሊያስተክትል የሚችላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣ | 2.4 ሚስጥር፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.4.1 ሚስጥርን ለመጠበቅ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች<br>2.4.2 ሚስጥርን አለመጠበቅ በሀገር ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች፣ | • ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የሚያውቁትን ሚስጥር ለመጠበቅ በእነሱ በኩል ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች እንዲወያዩ ማድረግ። ከኢኮኖሚ ጉዳዮች አንስቶ እስከ ፀጥታ ጉዳዮች ድረስ የሚዘልቁና በሚስጥርነት መያዝ ያለባቸው ነገሮች አሉ። ለምሳሌ በአንድ ቦታ አንድ የማዕድን ሀብት ቢገኝ መንግሥት ሙሉ በሙሉ የሀብቱን አጠቃቀምና አጠቃላይ ሁኔታ ግልጽ እስከሚያደርግ ሀብቱ የሚገኝበትን ሥፍራና የሀብቱን ዓይነትና ብዛት ማሳወቅ ተገቢ አይሆንም። ይህ በሚስጥርነት መያዝ የሚገባው ጉዳይ ሚስጥርነቱ ቢባክን ሀገሪቱን ለከፋ የኢኮኖሚና ለሌሎችም ጉዳቶች ሊያጋልጣት ይችላል። የተማሪዎቹን አቅም የሚመጥኑ ጉዳዮችን (Case Studies) በማቅረብ የሚስጥር መባከን በሀገር ደረጃ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ተማሪዎች ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ሙስናን ለመከላ ከል የዴሞክራሲ ያዊ ተቋማት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣<br>• ሙስናን በመከላከል ረገድ | 2.5 ሙስናን መከላከያ መንገዶች፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.5.1 ሙስናን የሚከላከሉ ዴሞክራሲያዊ | • በክለሳ መልክ የሙስናን አስከፊነት አስመልክቶ እያንዳንዱ ተማሪ አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ። በማስከተልም ተማሪዎ ቹን በቡድን በመክፈል ሙስናን በመዋጋት ረገድ የነሱ፣ የፍትህ አካላትና የሕብረተሰብ ሚና ምን መሆን እንደሚገባው ተወያይ ተው ለክፍል እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| የፍትህ አካላትንና የሕብረተሰብን ሚና ያብራራሉ፣<br>• በደረጃቸው የሙስናን ተግባራት ይታገላሉ፣ | ተቋማት አስፈላጊነት፣<br>2.5.2 ሙስናን በመከላከል ረገድ የፍትህ አካላት ሚና፣<br>2.5.3 ሙስናን በመከላከል ረገድ የሕብረተሰብ ሚና፣ | |

## ግምገማ

**ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።**

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ መካከል የሚታየውን የውጤት ልዩነት በማነፃር መሆን ይኖርበታል ።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥትና በክልል ሕገ መንግሥታት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ይዘረዝራሉ፣በሀገር ደረጃ ከተማሪ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣የሚያከናወኗቸውን ተግባራት ባላቸው መብት ዙሪያ ብቻ ይዘረዝራሉ።የሚስጥር መባከን በሀገር ደረጃ ሊያስተክትል የሚችላቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣ሙስናን ለመከላ ከል የዴሞክራሲ ያዊ ተቋማት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣ሙስናን በመከላከል ረገድ የፍትህ አካላትንና የሕብረተሰብን ሚና ያብራራሉ፣በደረጃቸው የሙስናን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥትና በክልል ሕገ መንግሥታት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ይተነትናሉ፣በሀገር ደረጃ ከተማሪ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አለመኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣የሚያከናወኗቸውን ተግባራት ባላቸው መብት ዙሪያ ብቻ ያደርጋሉ።የሚስጥር መባከን በሀገር ደረጃ ሊያስተክትል የሚችላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣ሙስናን ለመከላ ከል የዴሞክራሲ ያዊ ተቋማት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣ሙስናን በመከላከል ረገድ የፍትህ አካላትንና የሕብረተሰብን ሚና ያብራራሉ፣በደረጃቸው የሙስናን ተግባራት ይታገላሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 3. እኩልነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 10**

- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የተደነገጉ የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብቶች ያውቃሉ።
- የብሔሮች ብሔረሰቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን መብት አለመከበር የሚያስከትለውን ጉዳት ይረዳሉ።
- ሴቶችና ወንዶች በማንኛውም ሁኔታ እኩል መሆናቸውን ያውቃሉ።
- የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አካባቢያቸውን ለማስተዳደር ያላቸውን መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ። | 3.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች አካባቢያቸውን የማስተዳደር፣ መብት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>3.1.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች አካባቢያቸውን የማልማትና ከልማቱም እኩል የመጠቀም መብት አስፈላጊነት<br>3.1.2 ክልሎችን ከሀገር ልማት እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ፣ሰላምን ለማስፈንና ዕድገትን ለማፋጠን፣ | • ከፌዴራልና ከክልል ሕገመንግሥቶች ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን ስለማስተዳደራቸውና ስለልማት የሚያወሳውን እንዲረዱት ማድረግ። ዋናው ቁም ነገር በኢትዮጵያ የፌዴራል ሕገመንግሥት መሠረት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላቸውን የማስተዳደርና የማልማት መብት እንዳላቸው መረዳቱ ነው። ከዚህም በመነሳት ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የነዚህ መብቶች ባለቤት መሆናቸው የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲወያዩና ይህንኑ ለክፍል በማቅረብ የራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የእኩል ተጠቃሚ ነት መብት ካልኖረ የሚያስከትለውን ችግር ያብራራሉ፣ | 3.2 እኩል ተጠቃሚነት ካልኖረ የሚያስከትለው ጉዳት፣ (2 ክፍለ ጊዜ) | • ተማሪዎች መብቶቻችን ናቸው የሚሏቸውን ነገሮች እንዲዘረዝሩ ማድረግ። የጠቀሷቸው ነገሮች መብቶቻቸው የሚሆኑት ለምን እንደሆነ ምክንያት እንዲሰጡ ማድረግ። ለምሳሌ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የፈለጉትን የሙያ ሥራ የመሥራት መብት አላቸው። ይህ ሕገመንግሥቱ እውቅና የሰጣቸው መብቶች ናቸው። በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | -በዜጐች መካከል አለመግባባት መፍጠር፣<br>- የሰላም መደፍረስ፣<br>- የእድገት መጓተት፣ | በመከፋፈል መብቶቻችን ናቸው የሚሏቸው ነገሮች ሲጣሱና ሕጋዊ መፍትሔ ማግኘት ባይችሉ ምን እንደሚያደርጉ ተወያይተው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ፋይዳን ያብራራሉ፣ | 3.3 የብሔሮች፣የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.3.1 yኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎችና፣ ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች መከበራቸው የሚኖረው ጠቀሜታ፣ | • ከፌዴራል ሕገመንግሥት ስለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት የሚያወሳውን አንቀጽ 39ንና የመሳሰሉትን እንዲሁም ከክልል ሕገመንግሥት ተዛማጅ የሆኑ አንቀጾችን ተማሪዎቹ እንዲያነቧቸውና እንዲገነዘቧቸው ማድረግ። ከዚያም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የነዚህ መብቶች መከበር የሚኖረውን ጠቀሜታ በተመለከተ እንዲወያዩና ለክፍል በማቅረብ የጋራ ዳምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የጾታ እኩልነት መከበሩ የሚሰጠውን ጥቅም ይዘረዝራሉ፣ | 3.4 የጾታ እኩልነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.4.2 የጾታ ዕኩልነት የሚሰጠው ጥቅም፣<br>- ሴቶች ለተፋጠ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማድረግ፣<br>- ሴቶችን የልማት ተቋዳሽ | • በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች ተማሪዎቹ በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ። ከዚሁ ጋር የሕብረተ ሰቡ 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውን እንዲያውቁት ማድረግ። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ሴቶችን የማያሳትፍ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ጉዳዮች ውጤታማ ይሆናሉ ማለት አይቻልም። ስለሆነም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የጾታ እኩልነት መከበር ያለው ፋይዳ ላይ ተነጋግረው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | ለማድረግ፣ | |
| • የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ያከብራሉ፣ | 3.5 አካል ጉዳተኝነት፣<br>**(1 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.5.2 የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠው ጠቀሜታ፣<br>- የእኩልነትና የሀገር ፍቅር ስሜትን ማዳበር፣<br>- የጠባቂነትና የተረጂነት ስሜትን ማስወገድ፣<br>- ለልማት የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት፣ | • ተማሪዎች አካል ጉዳተኝነትን በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ። አካል ጉዳተኞች የሕብረተሰቡ አንድ አካል ናቸው። ስለሆነም እንደማንኛውም ሕብረተሰብ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል። ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር ለሀገርም ይሁን ለራሳቸው የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ እንዲወያዩና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሃይማኖት ዕኩልነት መብት አለመከበር የሚያመጣውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣ | 3.6 የሃይማኖት ዕኩልነት መብት አለመከበር የሚያመጣው ጉዳት፣<br>**(1 ክፍለ ጊዜ)** | |

## ግምገማ

**ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።**

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አካባቢያቸውን ለማስተዳደር ያላቸውን መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታይዘረዝራሉ።የእኩል ተጠቃሚ ነት መብት ካልኖረ የሚያስከትለውን ችግር ይዘረዝራሉ፣የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ፋይዳን ይዘረዝራሉ፣የጾታ እኩልነት መከበሩ የሚሰጠውን ጥቅም ይዘረዝራሉ፣የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ያከብራሉ፣የሃይማኖት ዕኩልነት መብት አለመከበር የሚያመጣውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አካባቢያቸውን ለማስተዳደር ያላቸውን መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ።የእኩል ተጠቃሚ ነት መብት ካልኖረ የሚያስከትለውን ችግር ያብራራሉ፣የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ፋይዳን ያብራራሉ፣የጾታ እኩልነት መከበሩ የሚሰጠውን ጥቅም ይዘረዝራሉ፣የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ያከብራሉ፣የሃይማኖት ዕኩልነት መብት አለመከበር የሚያመጣውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 4. ፍትሐዊነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 10**

- አድሎአዊ አሠራሮች መወገድ እንደሚገባቸው ይገነዘባሉ።
- የፍትህ መጓደል የሚያስከትላቸውን ችግሮች ያውቃሉ።
- የፍትህ አካላት አሠራርን ይረዳሉ።
- ማህበራዊ አገልግሎቶች ሁሉም ዜጎች በፍትህዊነት መጠቀም እንዳለባቸው ይገነዘባሉ።
- በሀገር ደረጃ የግብርን ጠቀሜታ ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • አድሎአዊ አሠራሮች መወገድ የሚችሉባቸውን መንገዶች ያብራራሉ፣ | 4.1 አድሎአዊነት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>4.1.1 አድሎአዊ አሠራሮች መወገድ የሚችሉባቸው መንገዶች፣<br>- በሕግ መሠረት ብቻ መሥራት፣<br>- በቅንነትና በታማኝነት መሥራት፣<br>- ዜጎችን በእኩልነት ማየት፣ | • ተማሪዎች አድሎአዊነት ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደሚገለጽ እንዲወያዩበት ማድረግ። በአድሎአዊነት ላይ መግባባት ከተደረሰ በኋላ ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የዘረዘሯቸው አድሎአዊ አሠራሮች እንዴት ሊወገዱ እንደሚችሉ እንዲወያዩባቸው ማድረግና ውጤታቸውን ለክፍሉ በማቅረብ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ውይይታቸው በይዘትነት በተጠቀሱት ጭብጦች ላይ እንዲያተኩር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። |
| • የፍትሐዊነት መጓደል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በልማት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ያብራራሉ፣ | 4.2 የፍትሐዊነት መጓደል፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>4.2.1 የፍትሐዊነት መጓደል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በልማት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ፣<br>- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ላይ እምነት ማጣት፣<br>- የዜግነት ድርሻን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆን፣ | • የፍትሐዊነት መጓደልን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን ( Case Studies) ለተማሪዎች በቡድን ከፍሎ መስጠት። እንደነዚህ ዓይነቶች የፍትህ መጣስ ሲያጋጥሙ እነሱ ምን እንደሚያደርጉና ውጤቱስ ምን እንደሚሆን ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡና ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | |
| • የፍትህ አካላት አሰራር ከማንኛውም ወገን ነፃ መሆን እንደሚገባው ያብራራሉ፣<br>• መብታቸው ሲጣስ ሕጋዊ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ፣<br>• ማንኛውም ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ያስረዳሉ፣<br>• ትክክለኛ ዳኝነትን ለማግኘት መታገል እንደሚገባ ያብራራሉ፣ | 4.3 የፍትህ አካላት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>4.3.1 የፍትህ አካላት አሰራር፣<br>- ከሌሎች ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን፣<br>- የፍትህ አሰጣጥ ወገናዊ አለመሆን፣<br>4.3.2 ፍትህ የማግኘት መብት፣<br>- ትክክለኛ ዳኝነት ለማግኘት መታገል፣<br>- ትክክለኛ ዳኝነት/ፍትሕ ሲጣስ መብትን በህግ ማስከበር፣ | • በይዘትነት የተዘረዘሩትን ነጥቦች ለተማሪዎች በቡድን ከፍሎ በመስጠት በጉዳዩ ላይ ተወያይተው የውይይታቸውን ጭብጥ ለክፍል እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ለምሳሌ በፌዴራሉ (ለምሳሌ አንቀጽ 79) እና በክልል መንግሥታት ሕገመንግሥቶች የሰፈሩትን የዳኝነት ሥልጣንን ተማሪዎች አንብበው እንዲገነዘቡ ማድረግ። ይህ አሰራር ቢጣስ የፍትህ አሰጣጥ ጉዳይ ምን መልክ ሊኖረው እንደሚችል እንዲወያዩና ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ። |
| • የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• መንግሥትና ሕብረተሰብ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማትን የማዳረስ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፣ | 4.4 ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>4.4.1 ማህበራዊ አገልግሎቶችና አስፈላጊነታቸው፣<br>4.4.2 ማህበራዊ አገልግሎቶች ለሁሉም ያለ አድሎ አገልግሎት መስጠታቸው የሚሰጠው ጥቅም፣<br>4.4.3 መንግሥትና ሕብረተሰብ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ ያላቸው ሚና፣ | • በይዘትነት የተመለከቱትን ጭብጦች ተማሪዎቹን በቡድን ከፍሎ መስጠትና በጉዳዩ ላይ ተወያይተው የደረሱበትን ውሣኔ ለክፍሉ በማቅረብ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ለምሳሌ የማህበራዊ አገልግሎቶች የሚባሉት ጤና፣ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ ናቸው። እነዚህን ማህበራዊ ሰጪ ተቋማት ማቋቋም ደግሞ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ሕብረተሰብ በይመለከተኛል ስሜት ማከናወን የሚገባው ጉዳይ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች ጉዳዮቹን እንዲህ እያነሱ እንዲወያዩ ማድረግ ያስፈልጋል። |
| • ግብር ኢንቬስትመንትን እንደሚደግፍና እንደሚያስፋፋ | 4.5 ግብር፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>- ለኢንቬስትመንት ዕድገትና | • ስለግብር አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ። የሚቻል ከሆነም በአካባቢያቸው ወደሚገኘው ግብር ሰብሳቢ ተቋም በመሄድ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| ይገልጻሉ፣<br>• ለክልሎች ፍትሐዊ እድገት ግብር የሚኖረውን ሚና ያብራራሉ፣<br>• የፌዴራልና የክልል የግብር ገቢን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣ | መስፋፋት የግብር ሚና፣<br>-በክልሎች ፍትሐዊ ዕድገት ላይ የግብር ሚና፣<br>-የፌዴራልና የክልል የግብር ገቢ ዓይነቶች፣ | የሚሰበስቡት ምን ምን ዓይነት ግብር እንደሆነና ግብሮቹን መጣል ያስፈለገበትን፣ እንዲሁም የተሰበሰበው ግብር የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ ጠይቀው ለክፍሉ እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** አድሎአዊ አሠራሮች መወገድ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣የፍትሐዊነት መጓደል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በልማት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ይዘረዝራሉ፣የፍትህ አካላት አሰራር ከማንኛውም ወገን ነፃ መሆን እንደሚገባው ይዘረዝራሉ፣መብታቸው ሲጣስ ሕጋዊ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ይዘረዝራሉ፣ማንኛውም ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ይዘረዝራሉ፣ትክክለኛ ዳኝነትን ለማግኘት መታገል እንደሚገባ ይገልጻሉ፣የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማት አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣መንግሥትና ሕብረተሰብ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማትን የማዳረስ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፣ግብር ኢንቬስትመንትን እንደሚደግፍና እንደሚያስፋፋ ይገልጻሉ፣ለክልሎች ፍትሐዊ እድገት ግብር የሚኖረውን ሚና ያብራራሉ፣ የፌዴራልና የክልል የግብር ገቢን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** አድሎአዊ አሠራሮች መወገድ የሚችሉባቸውን መንገዶች ያብራራሉ፣የፍትሐዊነት መጓደል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በልማት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ያብራራሉ፣የፍትህ አካላት አሰራር ከማንኛውም ወገን ነፃ መሆን እንደሚገባው ያብራራሉ፣መብታቸው ሲጣስ ሕጋዊ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ፣ማንኛውም ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ያስረዳሉ፣ትክክለኛ ዳኝነትን ለማግኘት መታገል እንደሚገባ ያብራራሉ፣የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣መንግሥትና ሕብረተሰብ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተቋማትን የማዳረስ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፣ግብር ኢንቬስትመንትን እንደሚደግፍና እንደሚያስፋፋ ይገልጻሉ፣ለክልሎች ፍትሐዊ እድገት ግብር የሚኖረውን ሚና ያብራራሉ፣ የፌዴራልና የክልል የግብር ገቢን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 5. **የሀገር ፍቅር**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ታሪክ ማወቅ የሚሰጠውን ጥቅም ይገነዘባሉ።
- የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ መያዝ እንደሚገባ ያውቃሉ።
- ድህነትንና ኋላቀርነትን መዋጋት አስፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ።
- የዜግነት መብት መከበር የሀገር ፍቅር ስሜትን እንደሚያዳብር ይረዳሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • የሀገርን፣ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን ማወቅ ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ግንባታ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣ | 5.1 ትክክለኛ የሆኑ የሀገርን፣ (**2 ክፍለ ጊዜ**) የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የህዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን በሚገባ ማወቅ ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ግንባታ የሚኖረው ጠቀሜታ፣ | • በቅድሚያ ተማሪዎች ስለታሪክ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ። ለምሳሌ ታሪክ በግለሰቦች የሚፃፍ በመሆኑ ፀሐፊዎቹ የፀሐፊ ሥነምግባር ያላቸውና በትክክለኛ ማስረጃ ላይ የሚመሰረቱ ካልሆኑ በቀር የሚፅፉትን ታሪክ ሊያዛቡ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ታሪኩ የተዛባበት ወገን ደግሞ ቅር ይሰኛል። ስለዚህ ለተማሪዎች ይህን ሃሳብ ማቅረብና በቡድን ተወያይተው ትክክለኛ የህዝብን ታሪክ ማወቅ የሚኖረውን ጠቀሜታ በተመለከተ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብቶች በእኩልነት መከበር ለሀገር ፍቅር መጐልበት እንዴት እንደሚያግዝ ያብራራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብቶች ያከብራሉ፣ | 5.2 የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብቶች በእኩልነት መከበር ለሀገር ፍቅር ግንባታ ያለው አስተዋጽኦ፣ (**2 ክፍለ ጊዜ**) | • ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት ሕገመንግሥቶች ውስጥ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች የተባሉትን እንዲዘረዝሯቸው ማድረግ። የነዚህ መብቶች መከበር ያለውን ፋይዳ (በተለይ የሀገር ፍቅርን ከማጐልበት አንፃር) ተወያይተው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ አለመያዝ | 5.3 የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ አለመያዝ በሀገር ደረጃ | • ተማሪዎች የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች የሚሏቸውን እንዲገልፁ ማድረግ። ለምሳሌ ትምህርት ቤት የጋራ መገልገያ ነው። ትምህርት ቤትን ማውደም ወይም |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| የሚያስከትላቸውን ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣ | የሚያስከትለው ጉዳት፣ (1 ክፍለ ጊዜ) | የትምህርት ቤት ንብረትን ማውደም ሌላ ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል። ያ ተጨማሪ ወጪ ለሌላ ልማት ሊውል ይችል የነበረ ሲሆን ይህባለመሆኑ በሀገር ላይ ጉዳትን ያስከትላል። ተማሪዎች እንዲህ የተለያዩ ነገሮችን አንስተው እንዲወያዩና እንዴት በሀገር ደረጃ ጉዳት እንደሚያስከትል የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣<br>• የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን በመረዳት ግዴታቸውን ይወጣሉ፣ | 5.4 የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራት፣(2 ክፍለ ጊዜ)<br>5.4.1 የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን ለማስወገድ ሊደረጉ የሚገቡ ጥረቶች፣<br>- ከማንኛውም አፍራሽ ተግባራት ራስን ማራቅ፣<br>- አፍራሽ ተግባራትን መታገል፣<br>- አፍራሽ ተግባራት ሲፈፀሙ ለፍትህ አካላት ማሳወቅ፣ | • ተማሪዎች በየተራ የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራት እንዴት ዓይነቶቹ እንደሆኑ እንዲገልጹ ማድረግ። ለምሳሌ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ጤናማ የመማር ማስተማር ሒደት እንዳይካሄድ ረብሻና ብጥብጥ የሚፈጥሩ ወገኖች አሉ። እነዚህን ወገኖች በመታገል በኩል ተማሪዎቹ ምን ጥረት ያደርጋሉ? እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማስቻል። |
| • የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎትን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣<br>• የደህነትና ኋላቀርነትን የመዋጋት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣<br>• ድህነትና ኋላቀርነትን ለማጥፋት የታቀዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና | 5.5 ድህነትንና ኋላቀርነትን መዋጋት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>5.5.1 ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማጥ ፋት የታቀዱ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለመተግበር ከመንግሥትና ከዜጐች የሚጠበቁ ግዴታዎች፣<br>5.5.2 ድህነትንና ኋላቀርነትን | • በመንግሥት የተዘረጉ የልማት ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎች ንና ዕቅዶችን ተማሪዎቹ እንዲያነቧቸው ማድረግ። እነዚህን ሰነዶች መሠረት በማድረግ ለዓላማዎቹ መሳካት በተለይ የነሱ ድርሻ ምን መሆን እንደሚገባው በቡድን ተወያይተው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• ድህነትን መዋጋት ለመንግሥት ወይም ለተወሰነ አካል የሚተው ተግባር አይደለም። በተለይም ዜጐች በበጐ ፈቃደኝነት መንፈስ በመነሳሳት ድህነትን መዋጋት ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ድህነት በአካባቢያቸው እንዴት እንደሚገለፅ እንዲወያዩና ድህነቱንም ለማስወገድ የበጐ ፈቃደኝነት አስፈላጊነትን በተመለከተ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| የልማት ዕቅዶችን ይገልፃሉ፣<br>• ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና የልማት እቅዶች ውጤታማ እንዲሆኑ ከመንግሥትና ከዜጐች የሚጠበቁ ግዴታዎችን ያብራራሉ፣ | ለመዋጋት በአካባቢ በበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ላይ መሳተፍ አስፈላጊነት፣ | ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የዜጐች መብት መከበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ያብራራሉ፣<br>• በዜግነት ያሏቸውን መብቶች ይዘረዝራሉ፣ | 5.6 ዜግነት (**1 ክፍለ ጊዜ**)<br>5.6.1 የዜጐችን መብት ማክበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ያለው ጠቀሜታ፣ | • ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው የዜጐች መብቶች የሚሏቸውን በመለየት እንዲወያዩና የእነዚህ መብቶች መከበር ለሀገር ፍቅር መዳበር እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ለክፍል ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ። |
| • ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገርን ፍቅር ለማዳበር እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ያብራራሉ፣ | 5.7 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፣<br>(**2 ክፍለ ጊዜ**)<br>5.7.1 ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገርን ፍቅር ለማዳበር የሚኖራቸው አስተዋጽኦ፣ | • ተማሪዎች ስለሀገር ፍቅር የሚሰማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ። በዚህ አረገድ ሰንደቅ ዓላማ የሀገርን ፍቅር እንዴት ሊያዳብር እንደሚችል የተቻላቸውን እንዲገልጹ ማድረግ። ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የኢትዮጵያን የሕዝብ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግና መዝሙሩን ሲዘምሩ ምን ስሜት እንደሚሰማቸው እንዲገልጹ በማድረግ ትምህርቱን ማጠናቀቅ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የሀገርን፣ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን ማወቅ ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ግንባታ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብቶች በእኩልነት መከበር ለሀገር ፍቅር መጐልበት እንዴት እንደሚያግዝ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብቶች ይዘረዝራሉ፣የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ አለመያዝ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፣የጋራ

የ8ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን በመረዳት ግዴታቸውን ይወጣሉ፣የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎትን አስፈላጊነትይዘረዝራሉ፣የደህነትና ኗላቀርነትን የመዋጋት አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣ድህነትና ኋላቀርነትን ለማጥፋት የታቀዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የልማት ዕቅዶችን ይዘረዝራሉ፣ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና የልማት እቅዶች ውጤታማ እንዲሆኑ ከመንግሥትና ከዜጐች የሚጠበቁ ግዴታዎችንይዘረዝራሉ፣የዜጐች መብት መከበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣በዜግነት ያሏቸውን መብቶች ይዘረዝራሉ፣ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገርን ፍቅር ለማዳበር እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የሀገርን፣ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪኮችና ባህሎችን ማወቅ ለአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት ግንባታ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፣የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብቶች በእኩልነት መከበር ለሀገር ፍቅር መጐልበት እንዴት እንደሚያግዝ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብቶች ያከብራሉ፣የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ አለመያዝ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፣የጋራ መገልገያ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣የሕዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሥጋት ላይ የሚጥሉ አፍራሽ ተግባራትን በመረዳት ግዴታቸውን ይወጣሉ፣የበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎትን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣የደህነትና ኋላቀርነትን የመዋጋት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ፣ድህነትና ኋላቀርነትን ለማጥፋት የታቀዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የልማት ዕቅዶችን ይገልፃሉ፣ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና የልማት እቅዶች ውጤታማ እንዲሆኑ ከመንግሥትና ከዜጐች የሚጠበቁ ግዴታዎችን ያብራራሉ፣የዜጐች መብት መከበር ለሀገር ፍቅር መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ያብራራሉ፣በዜግነት ያሏቸውን መብቶች ይዘረዝራሉ፣ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር የሀገርን ፍቅር ለማዳበር እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

## 6. የኃላፊነት ስሜት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍል ጊዜ 10**

- ቃል ኪዳንን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባሉ።
- የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት እንደሚገባ ያምናሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን መጠበቅና መንከባከብ ተገቢ መሆኑን ይገነዘባሉ።
- የሕዝብ ሀብትና ንብረትን መጠበቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ያውቃሉ።
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገር ላይ የሚያስከትላቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ለራስና ለሀገር የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• የኃላፊነት ድርሻን ሳይወጡ በመቅረት የሚከሰቱ ጥፋቶች በራስና በቤተሰብ ክብር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ይገልፃሉ፣ | 6.1 የኃላፊነት ድርሻን በብቃት ስለመወጣት፣<br>- ታአማኒነትን ማግኘት፣<br>- መወደድና መከበር፣<br>- እራስን ማሳደግ፣<br>- የሀገርን ልማት ማፋጠን፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>6.1.1 የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ያለው ጠቀሜታ<br>6.1.2 የኃላፊነት ድርሻን በብቃት አለመወጣት የሚያስከትለው ችግር፣<br>- በራስ ላይ፣<br>- በቤተሰብ ላይ፣ | - ተማሪዎች የኃላፊነት ድርሻን በደንብ እንዲገነዘቡ ንድፈ ሀሳባዊ የሆኑ ኃላፊነቶችን በቡድን ከፋፍሎ መስጠትና እነዚህን ኃላፊነቶች በብቃት ሲወጡ ለነሱም ሆነ ለሀገር ምን ጥቅም እንደሚያስገኙ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። ለምሳሌ አንዱ ቡድን የደረሰው ኃላፊነት የትምህ ርት ቤቱን ጽዳት መጠበቅ ሊሆን ይችላል። ይህ ቡድን ይህን ኃላፊነት ባግባቡ ከተወጣ በሌሎች ተማሪዎችና መምህራን ይወደዳል፣ ይከበራል። ከዚህም በላይ ትምህርት ቤቱ ምቹ የመማር ማስተማር የሚከናወንበት ይሆናል። ይህ ምቹ ትምህ ርት ቤትም የሀገሪቱን ልማት የሚያፋጥኑ ወጣቶች የሚፈሩበት ማዕከል ይሆናል። የኃላፊነት ድርሻን በብቃት አለመወጣት ንም በተመለከተ እንደዚሁ አንድ ጉዳይ (Case Study) በማቅረብ ተማሪዎቹ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ማንኛውም ድርጅት፣ መንግሥት፣ ግለሰብ ወዘተ የገባውን ቃል ኪዳን | 6.2 ቃል ኪዳንን ማክበር፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)** | - በክለሳ መልክ ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልፁ ማድረግ። በማስከተልም ለቡድኖች ጉዳዮችን (Case Study) በማቅ ረብ |

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| አክብሮ በተግባር መፈፀም እንዳለበት ይገልፃሉ፣<br>• ማንኛውም ድርጅት መንግሥት ወይም ግለሰብ ለሚያከናውነው ድርጊት ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበትና ጠቀሜታውንም ያብራራሉ፣<br>• የገቡትን ቃል ኪዳን ያከብራሉ፣ | - ማንኛውም ዜጋ ወይም ድርጅት ወይም መንግሥት ለገባው ቃልኪዳንና ለሚፈጽመው ድርጊት ኃላፊነትን የመውሰድ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣<br>- ቃል ኪዳንን አለማክበር በሀገር ደረጃ የሚያስከትለው ጉዳት፣ | ቃልኪዳንን የማክበር ኃላፊነትንና ጠቀሜታውን በተመለከተ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ።<br>• ለምሳሌ አንድ ድርጅት በመመስረቻ ሰነዱ ላይ በግልጽ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት በተቋቋመበት አካባቢ የሚገኘውን ድህነት ለመቀነስ እንደሚሰራ ያሳውቃል። ነገር ግን ይህ ድርጅት የአካባቢውን ሕዝብ ከመጥቀም ይልቅ የራሱን ሠራተኞች የሚጠቅም ከሆነ የገባውን ቃል ኪዳን አላከበረምና የህግም ሆነ የሞራል ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አለበት። የተቋቋመበትም ዓላማ ግቡን አይመታም። |
| • የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ | 6.3 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>6.3.1 የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት ፣<br>- የአካባቢ ብክለት፣<br>- የአየር ንብረት መዛባት፣<br>- ከቱሪዝም የሚገኝ ገቢ መቀነስ/መጥፋት፣ | - የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶችን ምንነት እንዲከልሱ ማድረግ። የሚቻል ከሆነ የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች እንዲበኙ ማድረግ። በጉብኝታቸውም የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች የሚሰጡትን ጥቅም በውል እንዲገነዘቡ ማድረግ። ጥቅሙን በደንብ ከተገነዘቡ ዘንዳ ለተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ሊደረግላቸው የሚገቡ እንክብካቤዎች ምን እንደሆኑና ይህን አለማድረግ የሚያስከትለውን ውጤት ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ፣ ውይይታቸው ወደተጠቀሱት ይዘቶች እንዲያተኩር ማድረግ አስፈላጊ ነው። |
| • ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስከትላቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ይዘረዝራሉ፣ | 6.4 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገር ላይ የሚያስከት ላቸው ኢኮኖሚያዊና | - ተማሪዎቹ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያውቁትን በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ። ከዚያም በቡድን በመከፈል በሽታው እያስከተለ ያለውን ችግር፣ እንዲሁም በሽታውን ለመከላከል ሊደረጉ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎችና የጋራ ጥረቶች አንስተው እንዲወያዩ በመጨረሻም የራሳቸውን ድምዳሜ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| • በሽታውን ለመከላከል ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችና የጋራ ጥረቶችን ያብራራሉ፣<br>• ራሳቸውን ከበሽታው ይጠብቃሉ፣ | ማህበራዊ ችግሮች፣<br>-በሽታውን ለመከላከል ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችና የጋራ ጥረቶች፣ | እንዲሰጡ ማድረግ። ከተቻለም በበሽታው የተጠቁ ታማሪዎችን በሆስፒታል ወይም ባሉበት ቦታ እንዲጐበኙ ማድረግና ግንዛቤያቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ለራስና ለሀገር የሚኖረውን ጠቀሜታን ይዘረዝራሉ፣የኃላፊነት ድርሻን ሳይወጡ በመቅረት የሚከሰቱ ጥፋቶች በራስና በቤተሰብ ክብር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ይዘረዝራሉ፣ማንኛውም ድርጅት፡ መንግሥት፣ ግለሰብ ወዘተ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ በተግባር መፈፀም እንዳለበት ይገልፃሉ፣ ማንኛውም ድርጅት መንግሥት ወይም ግለሰብ ለሚያከናውነው ድርጊት ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበትና ጠቀሜታውንም ይዘረዝራሉ፣የገቡትን ቃል ኪዳን ያከብራሉ፣የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣በአካባቢያቸው የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስከትላቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ይዘረዝራሉ፣በሽታውን ለመከላከል ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችና የጋራ ጥረቶችን ይዘረዝራሉ፣ራሳቸውን ከበሽታው ይጠብቃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የኃላፊነት ድርሻን በብቃት መወጣት ለራስና ለሀገር የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣የኃላፊነት ድርሻን ሳይወጡ በመቅረት የሚከሰቱ ጥፋቶች በራስና በቤተሰብ ክብር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ይገልፃሉ፣ማንኛውም ድርጅት፡ መንግሥት፣ ግለሰብ ወዘተ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ በተግባር መፈፀም እንዳለበት ይገልፃሉ፣ ማንኛውም ድርጅት መንግሥት ወይም ግለሰብ ለሚያከናውነው ድርጊት ኃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበትና ጠቀሜታውንም ያብራራሉ፣የገቡትን ቃል ኪዳን ያከብራሉ፣የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርሶችን አለመጠበቅ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣በአካባቢያቸው የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስከትላቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ይዘረዝራሉ፣በሽታውን ለመከላከል ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎችና የጋራ ጥረቶችን ያብራራሉ፣ራሳቸውን ከበሽታው ይጠብቃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 7. ጠንካራ የሥራ ባህል

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የሥራንና የጊዜን ክቡርነት ይገነዘባሉ።
- ለሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ መሆኑን ያውቃሉ።
- ህገመንግሥታዊ የልማትና ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ይረዳሉ።
- የሙያ ችሎታንና የሙያ ሥነምግባረን ማዳበር ለምርታማነትና ለዕድገት መሠረት መሆኑን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ውጤታማ ሥራ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• በሚያከናውኗቸው ተግባራት አርአያ ይሆናሉ፣ | 7.1 ውጤታማ ሥራ፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.1.1 ጊዜን ሳያባክኑ ጠንክሮ መሥራት፣<br>7.1.2 አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለአገር እድገት የሚኖረው ፋይዳ፣ | - አንድ ሥራ ውጤታማ ሥራ እንዲባል መመዘኛው ምን እንደሆነ ተማሪዎች በየተራ እንዲያብራሩ ማድረግ። ውይይታቸው እንዲገኝ የሚጠበቀውን ውጤት ያስገኘና በታቀደለት የጊዜ ገደብ ወይም ባነሰ የተሰራ ሥራ ነው ውጤታማ የሚባለው የሚለውን ማንፀባረቅ አለበት። እንዲሁም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረውን ፋይዳ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ለሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑንና ያለውንም ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• ለሚያከናወኗቸው ተግባራት ለሥራ የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ፣ | 7.2 ሥራን ዕቅድ አውጥቶ መሥራት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.2.1 ለሚያከናወኑት ሥራ የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ መጠቀም አስፈላጊነት፣ | - ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ዕቅድ እንዲያወጡ የተለያዩ ርዕሶችን መስጠት። ለምሳሌ በትምህርት ቤት የልማት ተግባር ላይ መሳተፍ፣ ወይም በአካባቢ የሚገኙ አቅመ ደካሞችን መርዳት ሊሆን ይችላል። ዕቅዶቹ ከተዘጋጁ በኋላ ሁሉም ተማሪ በእያንዳንዱ ቡድን ሥራ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ማድረግና ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑንና የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ፣ |
| • ሁሉም ሥራዎች እኩልና ሊከበሩ የሚገቡ መሆናቸውን ያስረዳሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸውና በቤታቸው ውስጥ ሥራን ሳይንቁ ይሠራሉ፣ | 7.3 ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መኖር፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.3.1 ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መኖር በግልና በሀገር እድገት ላይ የሚያሳድ | - በአካባቢያቸው ሳይሰሩ የሚኖሩ ወጣቶችን እንዲሁም በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን ሥራ ለምን እንደማይሰሩ አነጋግረው ያገኙትን መልስ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ማድረግ። ከዚህም ተነስተው ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መኖር መፈለግ ለግለሰቦቹም ሆነ ለሀገር ዕድገት የሚያመጣውን ጉዳት ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

የ8ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | ረው አሉታዊ ተፅዕኖ፣ | |
| • በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ለሀገር እድገት ያላቸውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣ | 7.4 የልማትና የኢኮኖሚ ዓላማዎች፣(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.4.1 በሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማት የኢኮኖሚና የባህል ነክ ዓላማዎች ለሀገር እድገት ያላቸው ጠቀሜታ፣ | - በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው ከሰነዱ ላይ እንዲያነቧቸውና በደንብ እንዲገነዘቧቸው ማድረግ። ከዚያም የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎቹ ለሀገር እድገት ያላቸውን ጠቀሜታ በተመለከተ በመምህሩ እየተደገፉ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ለጠንካራ የሥራ ባህል መጐልበት የሙያ ችሎታና የሙያ ስነምግባር መዳበር አስፈላጊ እንደሆኑ ይገልፃሉ፣ | 7.5 ጠንካራ የሥራ ባህል፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.5.1 ለጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር መዳበር ተገቢነት፣<br>7.5.2 ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆንና የሌሎችን የሙያ ውጤት ማድነቅ፣<br>- ከሌሎች በጐ ልምዶችን መቅሰም፣<br>- የሌሎችን የሙያ ውጤት ማድነቅ፣ | - ተማሪዎቹ የገባቸውን ያህል ጠንከራ የሥራ ባህል ምን እንደሆነና መገለጫዎቹን በየተራ እንዲገልጹ ማድረግ። ለምሳሌ ሥራንና የሥራ ሰዓትን አክብሮ ሥራን መሥራት ጠንካራ የሥራ ባህል መግለጫ ነው። የሠራተኛ ችሎታ ሁልጊዜ መሻሻል አለበት። አንድ ሰው ወንበር የሚሠራ ከሆነና ሁልጊዜ ወንበር እንጂ ሌላ የማይሰራ ከሆነ በፍፁም ሊሻሻል አይችልም። እንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮችን እያነሱ ተማሪዎች እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማስቻል። |

## ግምገማ

**ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።**

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ውጤታማ ሥራ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣በሚያከናውኗቸው ተግባራት አርአያ ይሆናሉ፣ለሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑንና ያለውንም ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣ለሚያከናወኗቸው ተግባራት ለሥራ የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ፣ሁሉም ሥራዎች እኩልና ሊከበሩ የሚገቡ መሆናቸውን ያስረዳሉ፣ በትምህርት ቤታቸውና በቤታቸው ውስጥ ሥራን ሳይንቁ ይሠራሉ፣ በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ለሀገር እድገት ያላቸውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣  ለጠንካራ የሥራ ባህል መጐልበት የሙያ ችሎታና የሙያ ስነምግባር መዳበር አስፈላጊ እንደሆኑ ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**ውጤታማ ሥራ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣አርአያነት ያለውና ለምስጋና የሚያበቃ ሥራ መሥራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በሚያከናውኗቸው ተግባራት አርአያ ይሆናሉ፣ለሥራ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑንና ያለውንም ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣ለሚያከናወኗቸው ተግባራት ለሥራ የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ፣ሁሉም ሥራዎች እኩልና ሊከበሩ የሚገቡ መሆናቸውን ያስረዳሉ፣ በትምህርት ቤታቸውና በቤታቸው ውስጥ ሥራን ሳይንቁ ይሠራሉ፣ በፌዴራል ሕገመንግሥት የተደነገጉ የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ለሀገር እድገት ያላቸውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣  ለጠንካራ የሥራ ባህል መጐልበት የሙያ ችሎታና የሙያ ስነምግባር መዳበር አስፈላጊ እንደሆኑ ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**8. ራስን መቻል**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 6**

- ራስን ከማንኛውም ዓይነት ጥገኝነት ማላቀቅና ለራስ ክብር መስጠት የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ፣።
- የኮንትሮባንድ ንግድን ጐጂነት ያውቃሉ።
- በራስ የመተማመን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • ከጥገኝነት ለመላ ቀቅ ሊደረጉ የሚገባ ቸውን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣<br>• ከጥገኝነት መላቀቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• የኮንትሮባንድ ንግድ አስከፊነትን ይገልፃሉ፣<br>• የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ያስረዳሉ፣ | 8.1 ከጥገኝነት መላቀቅ፣ (3 **ክፍለ ጊዜ**)<br>8.1.1 ከጥገኝነት ለመላቀቅ ለራስ ክብር መስጠት፣<br>8.1.2 ከጥገኝነት በመላቀቅ ራስን መቻል፣<br>8.1.3 ከጥገኝነት መላቀቅ ለኢኮኖሚያዊ ፣ለማህበራዊ እድገትና ለመልካም ዜጋ ግንባታ የሚያደርገው እገዛ፣<br>8.1.4 ኮንትሮባንድ እና የጥገኝነት ስሜት፣<br>- የኮንትሮባንድ ንግድ ሀገር አቀፍ ገጽታ፣<br>- የኮንትሮባንድ ንግድ ዓለም አቀፍ ገጽታ፣<br>-የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች | -ተማሪዎች ጥገኝነት ምን እንደሆነና በምን እንደሚገለጽ (ለምሳሌ በእነሱ ደረጃ) በየተራ እንዲያስረዱ ማድረግ። ከእንደዚህ ዓይነት የጥገኝነት ስሜት ለመላቀቅ ምን ሊደረግ እንደሚገባው፣ እንዲሁም ከጥገኝነት መላቀቅ የግለሰቡም ሆነ ለሀገር የሚኖረውን ፋይዳ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ። ከጥገኝነት ለመላቀቅ የሚያስፈልገው አንድ መሠረታዊ ነገር ለራስ ክብር መስጠት ነው። አንዳንድ ሰዎች እኔ ብልህ አይደለሁም፣ እኔ ጉበዝ አይደለሁም ወዘተ. እያሉ እራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ አሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በምንም ዓይነት ራሳቸውን ሊችሉና ከጥገኝነት ሊላቀቁ አይችሉም። ተማሪዎቻችንም ብቁ ዜጐች እንዲሆኑ በራሳቸው የሚተመመኑና በሌሎች ትከሻ ላይ ለመኖር ምንም ዓይነት ፍላጐት የሌላቸው ሊሆኑ ይገባል። ዜጐች ከጥገኝነት ተላቀው ራሳቸውን ሲችሉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ያድጋል። በዚህም የተነሳ ማህበራዊ ሕይወት ይሻሻላል ማለት ነው። ስለሆነም ቡድኖቹ በነዚህ ላይ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ።<br>- በሌላ በኩል አንድ የጥገኝነት መገለጫ የኮንትሮባንድ ንግድ ነው። ተማሪዎች በቀደሙት ክፍሎች ስለኮንትሮባንድ ንግድ እንዲያውቁ ተደርገዋል። እዚህ ላይ የሚያውቁትን በራሳቸው እንዲያስረዱ ማድረግ። ከዚያም የኮንትርባንድ ንግድ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ሀገር አቀፍና አለም ገጽታ እንዲሁም ይህን ሕገወጥ ንግድ ለመግታት እየተደረገ ያለውን ጥረት ማስረዳትና ተማሪዎች የንግዱን ሀገር ጐጂነት ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በራስ የመተማመን ስሜትን የማዳበር አስፈላጊነት | 8.2 በራስ መተማመን፣ (3 **ክፍለ ጊዜ**) | • ተማሪዎች በቀደመው ክፍለ ትምህርት እንደተማሩት አንድ ሰው በራሱ የሚተማመን እስከአልሆነ ድረስ በፍፁም ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም በራሱ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይገልፃሉ፣<br>• በራሳቸው የሚተማመኑ ይሆናሉ፣ | 8.2.1 በራስ የመተማመን ስሜትን ማዳበር አስፈላጊነት፣<br>8.2.2 በራስ መተማመን ለራስ፣ ለቤተሰብና ለሀገር እድገት ያለው ጠቀሜታ፣<br>-በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር የራስን ችሎታ ማወቅና ማበልፀግ፣<br>- የራስ የሆነ አመለካከትና እምነትን ይዞ በመጽናት ከሌሎችም ለመማር ዝግጁ መሆን፣ | የማይተማመን ሰው ምን ትክክለኛ ሥራ ቢሰራ እሱ የሰራው ሥራ ትክክለኛ ነው ብሎ ስለማያስብ ሁልጊዜ መንፈሱ ከጥገኝነት ስሜት ሊላቀቅ አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ምንም የጥሩ ዕውቀት ባለቤት ቢሆን፣ እንዲሁም ጥሩ በራስ የመተማመን ስሜት ቢኖረውም የራሱ ዕውቀትና እምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ለመማር ግን ዝግጁ መሆን ይኖርበታል። ሁሉን እኔ ብቻ አውቃለሁ፣ እኔ ያልኩት ብቻ ትክክል ነው ብሎ ድርቅ ማለት በራሱ ከሚተማመን ሰው የሚጠበቅ ባህሪ አይደለም። ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው እነዚህ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ከጥገኝነት ለመላ ቀቅ ሊደረጉ የሚገባ ቸውን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ከጥገኝነት መላቀቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የኮንትሮባንድ ንግድ አስከፊነትን ይገልፃሉ፣የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ይዘረዝራሉ፣በራስ የመተማመን ስሜትን የማዳበር አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣በራሳቸው የሚተማመኑ ይሆናሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**ከጥገኝነት ለመላ ቀቅ ሊደረጉ የሚገባ ቸውን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ከጥገኝነት መላቀቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣የኮንትሮባንድ ንግድ አስከፊነትን ይገልፃሉ፣የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ያስረዳሉ፣በራስ የመተማመን ስሜትን የማዳበር አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣በራሳቸው የሚተማመኑ ይሆናሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**9. የቁጠባ ባህል**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 4**

- የቁጠባ ባህልን ማዳበር አስፈላጊነት ይገነዘባሉ።
- በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ጠቃሚ መሆኑን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የቁጠባን ባህል ማዳበር አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• ቁጠባ ለሀገር ዕድገት የሚጫወተ ውን ሚና ይገለፃሉ፣<br>• በአቅማቸው ቆጣቢ ይሆናሉ፣ | 9.1 ቁጠባ፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.1.1 የቁጠባ ባህልን ማዳበር አስፈላጊነት፣<br>- ራስን ለመቻል፣<br>9.1.2 የቁጠባ ባህል መዳበር ለሀገር ዕድገት የሚኖረው ጠቀሜታ፣<br>- መዋዕለ ንዋይን ሥራ ላይ ማዋል፣<br>9.1.3 አባካኝና ኋላቀር ልማዶች ምንድናቸው? | • ለክለሳ በሚያገለግል መልኩ የቁጠባ ባህልን ማዳበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ። በቁጠባ ባህል ላይ ግልጽነት ከተጨበጠ በኋላ ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል የቁጠባ ባህልን ማዳበር ለግለሰቡም ሆነ ለሀገር የሚኖረው ጠቀሜታ ላይ ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። ለምሳሌ የቁጠባ ባህሉ የዳበረ ሰው ከተለያዩ ለብክነት ከሚዳረጉ ተግባራት የራቀ በመሆኑ ራሱን የቻለ እንዲሆን ያበቃዋል። በሌላ በኩል የቁጠባ ባህላቸው የዳበረ ዜጐች የቆጠቡትን ሀብት ኢንቬስት ስለሚያደርጉ የሀገር ዕድገት በዚህ ረገድ ይፋጠናል ማለት ነው። እንዲሁም በሀገር ደረጃና በአካባቢያቸውም ተጨባጭ ሁኔታ የብክነት ምንጭ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን አሰራሮች፣ አኗኗር ወዘተ በቡድናቸው ውስጥ ተወያይተው ጉጂነታቸው ላይ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ለሀገር እድገት የሚ ኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በእቅድና በአቅም ላይ ይመራሉ፣ | 9.2 በእቅድና በአቅም ልክ መመራት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>-በእቅድና በአቅም ልክ መመራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረው ጠቀሜታ፣ | • እቅድ ምን እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያብራሩ ማድረግ። ከዚህ በመነሳት በእቅድ መመራት ለሀገር ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ በቡድን ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። ለምሳሌ ቤተሰባቸው በእቅድ የሚመራ ከሆነ የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር የተወሰነ ይሆናል። ይህም የሕዝብ ብዛትን የተወሰነ በማድረግ ብሔራዊ የሀብት አጠቃቀምን የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋል። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት፡፡ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ፡፡በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባን ባህል ማዳበር አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣ቁጠባ ለሀገር ዕድገት የሚጫወተ ውን ሚና ይዘረዝራሉ፣በአቅማቸው ቆጣቢ ይሆናሉ፣እቅድና በአቅም ልክ መመራት ለሀገር እድገት የሚ ኖረውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በእቅድና በአቅም ላይ ይመራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**የቁጠባን ባህል ማዳበር አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣ቁጠባ ለሀገር ዕድገት የሚጫዌወተ ውን ሚና ይገለፃሉ፣በአቅማቸው ቆጣቢ ይሆናሉ፣እቅድና በአቅም ልክ መመራት ለሀገር እድገት የሚ ኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በእቅድና በአቅም ላይ ይመራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

**10.ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 5**

- በአካባቢና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- የልዩ ልዩ ህብረተሰብ ክፍሎች መደራጀትና መጠናከርን ጠቀሜታ እንዳለው ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸ ውና በአካባቢያቸው የልማት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ። | 10.1 በአካባቢ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንቅስቃሴ ውስጥ የዜጐች ንቁ ተሳትፎ ወሳኝነት፣ **(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>10.1.1 የዜጐች ንቁ ተሳትፎ ወሳኝነት ለዴሞክራሲ ገግንባታ ለጋራ መግባባትና ለመልካም አስተዳደር መስፈን፣<br>- ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣<br>- ለፈጣን ልማት፣<br>- ለድህነት ቅነሳ፣<br>- ለመልካም አስተዳደር፣<br>- የጋራ መግባባት ለመፍጠር፣<br>- ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ፣<br>10.1.2 የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ለድህነት ቅነሳና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ፣<br>10.1.3 የዜጎች ንቁ ተሳትፎ ግልፅነትነና ተጠያቂነትን ለማስፈን | - የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ጽንሰ ሀሳብን ተማሪዎች በደንብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ እንዲያስችል ጽንሰ ሀሳቡን በውይይት እንዲከልሱ ማድረግ። ከዚያም በይዘትነት የተዘረዘሩትን ነጥቦች ለቡድኖች ከፋፍሎ በመስጠት እንዲወያዩበት ማድረግ። ለምሳሌ በትምህርት ቤት ውስጥ የማይገቡ ተግባራት ሲፈፀሙ መምህራ ንም ተማሪዎችም ካልተቃወሙ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር ሊሰፍን አይችልም። በዚህ መልኩ ሁሉንም ይዘቶች በተመለከተ ተማሪዎቹ እንዲወያዩና የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ። ቡድኖቹ የደረሱባቸውን ጭብጦች ለክፍል ውይይት በማቅረብ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በሲቪክስ ማህበራት ክበባት መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ | 10.2 ሲቪክ ማህበራት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>10.2.1 በሲቪክ ማህበራት መሳተፍ ለሀገር | - የሲቪክ ማህበራት ክበባትምንነት ላይ ተማሪዎች አስተያየታቸ ውን እንዲሰጡ ማድረግ። ከዚያም ተማሪዎቹን በቡድን በመክ ፈል በይዘትነት የሰፈሩትን ነጥቦች |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ያብራራሉ፣<br><br>• በትምህርት ቤታቸው የሲቪክ ማህበራት/ክበባት ይሳተፋሉ፣ | ልማት የሚኖረው ጠቀሜታ፡<br>- ለልማት፣ ለሰላምና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽ ለማድረግ፣ ለማትጋትና ለመቆጣጠር፣<br>10.2.2 በወቅታዊ ጉደዮች ላይ መንግስትን ለማትጋትና ለመቆጣጠር በሲቪክ ማህበራት መደራጀት፣ | ከፋፍሎ በመስጠት እንዲወያዩ ባቸው ማድረግ። ለምሳሌ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን በተመለከተ ሲቪክ ማህበራት ራሳቸው በጥበቃው ከመሳተፋቸው ባሻገር መንግሥት ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ፖሊሲዎችንና ሕችን እንዲያ ወጣ ማህበራቱ በሰላማዊ ሰልፍ ወዘተ መንግሥት ላይ ጫና ሊያደርጉ ይችላሉ። ቡድኖቹ እንዲህ የተወያዩባቸውን ውጤቶች ለክፍሉ በማቅረብ አጠቃላይ ተማሪው የራሱን ድምዳሜ እንዲሰጥ ማድረግ። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸ ውና በአካባቢያቸው የልማት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ።በሲቪክስ ማህበራት ክበባት መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሲቪክ ማህበራት/ክበባት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸ ውና በአካባቢያቸው የልማት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ።በሲቪክስ ማህበራት ክበባት መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሲቪክ ማህበራት/ክበባት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል

11. **ዕውቀትን መሻት**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- ዕውቀት የሚዳብርባቸውን መንገዶች ያውቃሉ።
- ዕውቀት አገልግሎት ላይ የሚውልባቸውን መንገዶች ያውቃሉ።
- የመረጃ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን መዋጋት ተገቢ መሆኑን ይረዳሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • ዕውቀት የሚዳብርባቸው መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በዕውቀት ማዳበሪያ መንገዶች በመገል ገል ዕውቀታቸውን ያዳብራሉ፣ | 11.1 ዕውቀት የሚዳብርባቸው መንገዶች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- መደበኛ ትምህርት፣<br>- መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣<br>- መገናኛ ብዙሀን፣<br>- የንባብ ባህልን ማዳበር፣ | - ተማሪዎች ዕውቀት ምን እንደሆነና ጠቀሜታውን እንዲያብራሩ ማድረግ። ከዚያም በቡድን በመክፈል በይዘትነት የተሰጡ እርእሶች ላይ እንዲወያዩ በማድረግና ለክፍሉ በማቅረብ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። ለተማሪዎቹ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ዕውቀት ከትምህርት ቤት ብቻ የማይገኝ መሆኑን ነው። |
| • ዕውቀት ለምርምር፣ ለፈጠራ ራስን ለማሻሻልና ለሀገር ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣ | 11.2 ዕውቀት አገልግሎት ላይ የሚውልባቸው መንገዶች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>-ለምርምር<br>-ለፈጠራ<br>-እራስን ለማሻሻል፣<br>-ለሀገር እድገት፣ | - ተማሪዎችን የዕውቀት መጨረሻ የት እንደሆነ በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ። ዕውቀት መጨረሻ ያለው ማህበራዊ ክንዋኔ አይደለም። በየቀኑ አዳዲስ ዕውቀቶች ይፈጠራሉ። ከነዚህ አዳዲስ ዕውቀቶች ጋር አብሮ መሄድ እስካልተቻለ ድረስ የራስ መሻሻልም ሆነ የሀገር ዕድገት የሚታሰቡ ጉዳዮች አይሆንም። አዲስ ዕውቀት በምርምር ይፈጠራል። ይህ አዲስ ዕውቀትም አዲስ ነገር ለመፍጠር ያስችላል። አዲስ ነገር በተፈጠረ ቁጥር የግለሰብም የሀገር ኑሮ ይሻሻላል። ስለሆነም ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ዕውቀት አገልግሎት ላይ በሚውልባቸው መንገዶች ላይ ተወያይተው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • በመረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮች ሊያደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ያብራራሉ፣<br>• ለሚያከናውኗቸው ተግባራት | 11.3 በመረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**) | - መረጃ የሌላቸውና ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮችን (Case Studies) ለተማሪዎች ማቅረብ። ለምሳሌ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በፈተናቸው መቶ በመቶ ካላመጡ ወደ ሁለተኛ ደረጃ እንዳያልፉ ተወሰነ የሚል። ቡድኖቹ በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡና አጠቃላይ ተማሪዎችም በመረጃ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| ሁሉ መረጃን ይጠቀማሉ፣ | | ያልተደገፈ ማንኛውም ነገር ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማስወገጃ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ይታገላሉ፣ | 11.4 ኋላቀር አስተሳሰቦችና አመለካከቶች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>-ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማስወገጃ መንገዶች፣<br>- ማንኛውንም አስተሳሰ ቦቻችንና አመለካከቶ ቻችንን በምክንያታዊነ ትና በማስረጃ ላይ መመስረት፣ | - ተማሪዎች በአካባቢያቸውም ይሁን ወይም በሌላ ቦታ የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት መገለጫዎች ናቸው የሚሏቸውን እንዲገልጹ ማድረግ። ለምሳሌ ተማሪ ጥሩ ውጤት ያላመጣሁት እከሌ ስለሚመቀኘኝ ነው ብሎ ማሰብ። እንደነዚህ ዓይነት አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በተማሪዎቹ ከቀረቡ በኋላ እነዚህን አስተሳሰቦችና አመለካከቶች እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸ ውና በአካባቢያቸው የልማት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ።በሲቪክስ ማህበራት ክበባት መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሲቪክ ማህበራት/ክበባት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች**በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸ ውና በአካባቢያቸው የልማት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ።በሲቪክስ ማህበራት ክበባት መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሲቪክ ማህበራት/ክበባት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል
ዕውቀት የሚዳብርባቸው መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣በዕውቀት ማዳበሪያ መንገዶች በመገል ገል ዕውቀታቸውን ያዳብራሉ፣ዕውቀት ለምርምር፣ ለፈጠራ ራስን ለማሻሻልና ለሀገር ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በመረጃ ያልተደገፉ ጉዳዮች ሊያደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ያብራራሉ፣ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ መረጃን ይጠቀማሉ፣ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማስወገጃ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣በአካባቢያቸው ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ይታገላሉ፣